«እንኳን ለብርሃነ ትንሣዔው በሰላም አደረሳችሁ»

ፕሬስ የሕዝብ ዘብ ነው

# ጦቢያ

ጦቢያ 12ኛ ዓመት ቁጥር 9 ሚያዝያ 22 1997




## ዶ/ር ነገደ ጐበዜ እንዲህ ይላሉ

ልዩ ቃለ- ምልልስ

«ጦቢያ» መጽሔት ከሚያዝያ 1984 ጀምሮ በየወሩ የሚታተም፣
በአጠቃላይ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር መጽሔት ነው::
መጽሔቱ ከማናቸውም የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ያልወገነና የግለሰቦችን
ነጻ አስተያየት የሚያስተናብር ነው::

አሥራ ሁለተኛ ዓመት፣ ቁጥር 9፣ ሚያዝያ 22 1997

## ኢትዮጵያን ወደ ትክክለኛ ሀዲድ ለመመለስ

«...እነዚህን በጥቂቱ ተጨልልፈው የቀረቡትን ችግሮች ለመፍታት ምንድነው መደረግ ያለበት? የማነውስ ኃላፊነት? የኢትዮጵያዊያንን ችግር የሚያውቅና የሚፈታ ኢትዮጵያዊ ማነው? የሚሉትን ጥያቄዎች በምርጫ አፋፍ ላይ ቆመን ከምናነሳቸው ዐበይት ጥያቄዎች መካከል ዋናዎቹ ይመስሉኛል»

ዳንዴው ሠርቤሎ ገጽ 4

## የኦሮሞ ጉዳይ... ወደዬት፣ ወደዬት?

«...ቀሪው ኢትዮጵያዊ ፍላጐቱ የሚረካውና ልቡ የሚረጋው፣ ልክ እንደእነዚህ ሁለቱ የኦሮሞ ድርጅቶች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት በቅድሚያ ይጠበቅለት የምትለዋን ጥያቄ ከፕሮግራሙ ሰርዞ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት መቆሙን በማያወላውል አኳኋን ሲያረጋግጥ ነው:: ለውጥ የለም ባዮችም ዋና መከራከሪያ ነጥባቸው ይኸው ጉዳይ ነው::»

ሐሰን ዑመር አብደላ ገጽ 11

## ኡኡታ አለኝ ለአገር ሙጥኝ!

«...እኛ ኢትዮጵያውያን፣ እንደዓለም ሕዝቦች ሁሉ የሰው ዘር ልጆች ነን ብለን ከተነሳን ግን፣ ዓይናችንን፣ ወኔአችንን፣ አእምሮአችንን፣ መንፈሳችንንና ሕሊናችንን ከወያኔ ላይ፣ ለአንዲት ደቂቃም እንኳን ማንሳት የለብንም::»

ክቡር ሎሬት ብላቴን ጌታ ፀጋዬ ገ/መድኅን ገጽ 22

## ቃለ መጠይቅ

«...በዚህ መጽሐፍ ሳቢያ በኢሕአዴግ መሪዎች አካባቢ የተያዘውን ክብርክ የሚዋሰን ፕሮፓጋንዳ ስታዘብ ያኔ «ከባሩድ ይልቅ ብዕር የሚያስበረግገው ኃይል» ብለን የተቸነው ትዝ አለኝ:: «በማያውቅቡትና ግራ በሚጋባበት» ሰላማዊ የትግል ስልት መፋለም የሚለው መስመር ምን ያህል ትክክለኛ እንደሆነ ከዚያን ጊዜ ይበልጥ ዛሬ ለመረዳት ችያለሁ:: ...ከዶክተር ነገደ መጽሐፍ ተብሎ የተጠቀሰው ከአቶ በረከት ጭንቅላት እንጂ ከእኔ መጽሐፍ የተወሰደ አይደለም:: አሳፋሪ ቅጥፈት ተጨምሮበታል::»

ዶክተር ነገደ ጎበዜ ገጽ 7

## ልዩ ጥንቅር

«... እንደዜጋ ሁኔታዎችን ሳጤን ካለፉት ዓመታት በጣም የተሻለ የተወዳዳሪ ፓርቲዎች ኃይል የሚታይበት ይሆናል ብዬ እገምታለሁ:: በጥቅል ግን ይኼ ፓርቲ አሸንፎ ሥልጣን ይይዛል ለማለት ያስቸግረኛል:: በአንድ ነገር ግን እርግጠኛ ነኝ:: ፓርላማው እንዳለፈው አንድ ሃሳብ ቀርቦ እጅ የሚወጣበት ፓርላማ ከመሆን የሚድን ይመስለኛል::

ተ/ፕሮፌሰር አያሌው ገጽ 16

## ተመልካች

«... ተማሪው በፈተና ወደቅሁኝ ከማለት ፋንታ መምህሩ ጣለኝ ካለ፣ መምህሩም የሚያዳላ ከሆነ፣ የተማሪ አመዳደቡ፣ ለተማሪዎች የሚቀርቡ መሣሪያዎችና አገልግሎቶች ወገናዊነትንና ጎሣዊነትን የሚያንፀባርቁ ከሆነ፣ የመምህራን ቅጥር፣ አመዳደብ፣ ዕድገት፣ የትምህርት ዕድል ማግኘት የብሔር ማንነትን የሚከተል ከሆነ የትምህርት ሥርዓቱ በስብሷል ወይም ፈርሷል ማለት ይቻላል::»

ወገኔ ገረሱ ገጽ 33

### ሌሎች

◆ ከመልዕክት ሣጥናችን 2፣ ◆ ከአዘጋጁ ቢሮ 3 ◆ ልዩ ጥንቅር 16 ◆ የቋንቋ ቃና 19
◆ የመነጋገሪያ መድረክ 14 ◆ ሕይወታችንን እንታደጋት 20 ◆ ሙሻዘር 25
◆ ማኅበራዊ ኪን 26 ◆ ምርጫ 97 29 ◆ ማኅበረሰብ 35 ◆ ቅኝት 37

✉ 22373 ☎ 23-26-04
ፋክስ:- 251-1-23-26-05
E-mail Address.
akpac @telecom.net.et
የባንክ ሂሳብ ቁጥር 3167
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣
አዲስ አበባ ቅርንጫፍ፣ አዲስ አበባ

**ዋና ሥራ አስኪያጅ**
ግርማ ፈይሣ
09/20-76-21

**ዋና አዘጋጅ**
አረጋ ወልደቂርቆስ

**ም/ዋና አዘጋጅ**
አጥናፉ ዓለማየሁ

**ሪፖርተሮች**
ሁሴን ከድር
መሰንበት ኃይሉ

**ኮምፒዩተር ቅንብር**
አረጋሽ ፀጋዬ

**ኮምፒዩተር ጽሁፍ**
አዲስዓለም ደምሴ
ሲያባራ ወልዴ

**ማስታወቂያ፣ ሽያጭና ሥርጭት**
ሙሉጌታ ወ/ሚካኤል
09/67-09-91
ዳንኤል ወርቅነህ

የፊት ገጽ ሽፋን ዲዛይን (አክፓክ)

**አሳታሚ**
አጥቢያ ኮከብ የኅትመትና የማስታወቂያ ሥራ
ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር
**አክፓክ**

# ቃለ - መጠይቅ



# «አሳፋሪ ቅጥፈት ተጨምሮበታል»

*ዶ/ር ነገደ ጐበዜ*

*«ሕገ መንግሥት ምርጫና ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ (ከትናንት ወዲያ እስከ ነገ)» በሚል ርዕስ ዶ/ር ነገደ ጐበዜ በቅርቡ ያሳተሙት መጽሐፍ አነጋጋሪ የፖለቲካ አጀንዳ ሆኗል። በተለይም የካቲት 20/1997 በቴሌቪዥን በቀረበ የፖለቲካ ክርክር ወቅት የማስታወቂያ ሚኒስትሩ ክቡር አቶ በረከት ስምዖን መጽሐፉን ለተመልካች እያሳዩ ተቃዋሚዎች ከተሸነፉ ውጤቱን አንቀበልም በማለት በዶ/ር ነገደ በተቀየሰ ስትራቴጂ መሠረት ረብሻ ለማስነሳት አይመለሱም የሚል ማስታወቂያ ከተናገሩበት ወዲህ መጽሐፉን የሚሻማው አንባቢ ቁጥር ቀላል አይደለም።*

*የተለያዩ አስተያየቶችና ግምገማዎችም በዚሁ መጽሔትና በሌሎችም ጋዜጦች ላይ ታትመዋል። የጦቢያ መጽሔት አንባቢያን የደረሰውን ማብራሪያ ቢያገኙ የየራሳቸውን ምዘና ሊሰጡ ይችላሉ በሚል እምነት ከዶ/ር ነገደ ጋር ያደረግነው ቃለ መጠይቅ ወምልልስ እንደሚከተለው ቀርቧል።* ⇨

ጦቢያ:- አቶ በረከት ስምኦን ባለፈው የካቲት 20 ተቃዋሚዎች በምርጫው ማግሥት ውጤቱን አሻፈረን ብለው አመጽ ለማስነሳት በዶ/ር ነገደ በተቀየሰ ስትራቴጂ መሠረት እየተንቀሳቀሱ ነው ብለዋል:: በመጽሐፍዎ አሁን ሕዝቡ እንዳየው ስለ ምርጫ ስትራቴጂ ሲያትቱ የምርጫውን ሂደት «ቀጣይነትና ተአማኒነት ያለው አገር አቀፍ እንቅስቃሴ ለመቀስቀስ እንጠቀምበት» ይላሉ:: ይህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ አቶ በረከት ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንዳሉት የትጥቅ ትግልን ይጨምራል ማለት ነው?

ዶ/ር ነገደ:- አይጨምርም:: እንዲያውም የኢሕአዴግ መሪዎች በጣም የተጨነቁት በመኢሶን የተጠቆመው የትግል ስትራቴጂ በምንም ዓይነት የትጥቅ ትግልን ሳያካትት አስተማማኝ የሆነ ሰላማዊ ጎዳና ስለሆነ ነው:: አመጽ፣ አመጽ እያሉ የሚጮሁት እነሱ በሕዝባችን ሰላማዊ ትግል ላይ በአመጽ ለመነሳት ሰበብ ስለሚፈልጉ ብቻ ነው:: በእርግጥ «የትጥቅ ትግል» ብንል ኖሮ መልሳቸው የተኩራራ «መንገዱን ጨርቅ ያርግላችሁ» የሚል ዲስኩር ነበር የሚሆነው:: ልክ ያዛሬ አምስት ዓመት መኢሶን «በቀስተ ደመና ሬዲዮ» አንድ ትችት እንዳስነበበ ትዝ ይለኛል:: ወቅቱ አንዳንድ ተቃዋሚዎች «ምርጫ የሚሉት ነገር አይሰራም:: ወያኔን በሚገባው ቋንቋ ማነጋገር ያስፈልጋል» የሚል ግልፅ አቋም ይዘው የሚንቀሳቀሱበት ወቅት ነበር:: ብዙ ቅን ወገኖቻችንም እንደዚሁ «ይህንን በአመጽ ሥልጣን ይዞ በአመጽ የሚገዛ ኃይል በመጻፍ፣ በመሰለፍ፣ ተቃውሞ በማሰማት ማስወገድ አይቻልም:: የትጥቅ ትግል አይቀሬም አስፈላጊም ነው» የሚል አስተሳሰብ ነበራቸው:: ይህንን አካሄድ በመቃወም «ወያኔን በማይገባው ቋንቋ ለመፋለም» በሚል ርዕስ ባቀረብነው ትችት ላይ ይህንን «ከባሩድ ይልቅ ብዕር የሚያስበረግገው» ብለን የጠራነውን ኃይል እንዴት እንታገለው ለሚለው ጥያቄ ስንመልስ «ወያኔን በሚገባው ቋንቋ ሳይሆን በማይገባው፣ በማያውቅበት፣ በማይፈቅደው፣ በሚፈራውና ግራ በሚጋባበት ሕዝባዊ የፖለቲካ ትግል» መፋለም እንደሚያስፈልግ በግልጽ አስቀምጠን ነበር:: በዚህ መጽሐፍ ሳቢያ በኢሕአዴግ መሪዎች አካባቢ የተያዘውን ክብርክ የሚዋሰን ፕሮፓጋንዳ ስታዘብ ያኔ «ከባሩድ ይልቅ ብዕር የሚያስበረግገን ኃይል» ብለን የተቸነው ትዝ አለኝ:: «በማያውቅበትና ግራ በሚጋባበት» ሰላማዊ የትግል ስልት መፋለም የሚለው መስመር ምን ያህል ትክክለኛ እንደሆነ ከዚያን ጊዜ ይበልጥ ዛሬ ለመረዳት ችያለሁ::

የኛ አቋም እንደዚህ ግልጽ ሆኖ ሳለ እነሱም አሳምረው እያወቁት እነ አቶ በረከት በቴሌቪዥን መጽሐፌን የጠቀሱ እየመሰሉ እኔን ደግሞ በማላውቅበት፣ በማልፈቅደው ምናልባትም ሞክሬው ስለማላውቅ ግራ በምጋባበት የትጥቅ ትግል ጎዳና ተሰማሪና አሰማሪ አድርገውኛል:: «የጠቀሱ እየመሰሉ» ያልኩት አውቄ ነው:: በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ዜጎች በሬዲዮና በቴሌቪዥን ከዶ/ር ነገደ መጽሐፍ ተብሎ የተጠቀሰው ከአቶ በረከት ጭንቅላት እንጂ ከኔ መጽሐፍ የተወሰደ አይደለም:: አሳፋሪ ቅጥፈት ተጨመሮበታል:: እሳቸው በጠቀሱት በመጽሐፉ ገጽ 173 ላይ ስለ ሕገ መንግሥት መቀየር ሂደት ሳትት:-

«በኛ አገር የሄድን እንደሆነ የንጉሡ ሕገ መንግሥት የተቀየረው በመሬት አንቀጥ-ቅጥ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ፣ የደርጉ ሕገ መንግሥት የተሻረው በጦር ሜዳ ሽንፈት እንደሆነ እናያለን:: አሁንም የኢሕአዴግን ሕገ መንግሥት ለማሻሻል ሳይሆን ጨርሶ ለመቀየር እንታገላለን ካልን ብዙ አማራጮች የሉንም:: ወይ በምርጫ እንቅስቃሴ ሳቢያ ሕዝባዊ ማዕበል አስነስተንና ኢሕአዴግን ከሥልጣን አስወግደን ለዚህ ለውጥ ሁኔታዎችን እናመቻቻለን:: ወይ ደግሞ የነፃና ፍትሃዊ ምርጫ በሮች በመዘጋታቸው ለዚህ ዓላማችን በሥራ ማቆም አድማ፣ በመሬት አንቀጥቅጥ ሰላማዊ ሰልፎችና በተለያዩ «የሲቪል ዲስኦቢዲያንስ» ታክቲኮች በመጠቀም...» እያልኩ የተነተንኩበት የሰላማዊ፣ የሕጋዊና የዴሞክራሲያዊ ትግል ስትራቴጂ መፈናፈኛ አልሰጣቸውም:: በተራ ማጭበርበር ተሰማርተው አንዳንዴ በመጽሐፉ የሌለ ሙሉ አረፍት ነገር እየጨመሩ ያልተጻፈ አንብበዋል:: በአዲስ ዘመን መጋቢት 7 ቀን በወጣው እትም ላይ እንዳየሁት አቶ በረከት ሲጠቅሱኝ የሚሉት:-

«...አሁንም የኢሕአዴግን ሕገ መንግሥት ለማሻሻል ሳይሆን ጨርሶ ለመቀየር እንታገላለን ካልን ብዙ አማራጮች የሉንም:: ያለን አማራጭ የትጥቅ ትግል ነው:: ወይ በምርጫ እንቅስቃሴ ሳቢያ...» እያሉ ትጥቅ ትግል የሚለውን ዓረፍተ ነገር ራሳቸው ጨምረው የቀረውን ክፍል ትንሽ ክፍ ተብሎ እንደተጠቀሰው ያነቡታል:: ከዚያ ሩቅ ሳይሄዱ እንደገና ያዳልጣቸዋል:: በዚሁ ጥቅስ ውስጥ «በሥራ ማቆም አድማ፣ በመሬት አንቀጥቅጥ ሰላማዊ ሰልፎችና በተለያዩ «የሲቪል ዲስኦቢዲያንስ» ታክቲኮች...» የሚለውን አቶ በረከት ማንም ሳይጠይቃቸው ተርጉመው «... በተለያዩ የአመፅ ታክቲኮች...» ብለው አንብበውታል::

በተራ የመሸታ ቤት ውይይት ሳይሆን በሚሊዮን በሚቆጠሩ ዜጎች ፊት፣ በተራ ግለሰብ ሳይሆን ምናልባት የዚህ መንግሥት ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ ሊባሉ በሚችሉ «ትልቅ ሰው» እንዲህ ዓይነቱን ተራ ማጭበርበር ስታዘብ በእውነቱ በዚች አገራችን እያንሰራራ ያለው ከፍተኛ የሞራል ውድቀትና በሕብረተሰባችን የተከሰተው የባህላዊ እሴቶች መፍረክረክ ምን ያህል ሥር እየሰደደ መሆኑን ገምቼ በጣም ነው ያዘንኩት:: ትግላችን ከተርታ የሥልጣንና የፖለቲካ ትግል አልፎ እልህ አስጨራሽ የሚሆን የሞራልና የኢትዮጵያዊ እሴቶች መልሶ ለመገንባትም የሚደረግ ትግል መሆን እንደሚኖርበት ከመቸውም ይበልጥ ግልጽ አድርጎልኛል::

ለማንኛውም ሴራ ብሎ ነገር የለም:: ዶሮ ብታልም ያን ጥሬዋን ሆኖ ነው እንጂ እንዲያውም መጽሐፉ እስከዚህም ስለ ቀጣዩ ምርጫ ሳይሆን ስለቀጣዩ ክፍለ ዘመን የሀገራችንና የሕዝባችን እጣ ፈንታ ከወለደው ጭንቀት ተነስቶ የተጻፈ መጽሐፍ ነው:: በነገው በግንቦት ብቻ ሳይሆን በዚህ መድበለ ፓርቲ ምርጫ በማይፈቅድ የኢሕአዴግ ስታሊናዊ ሕገ መንግሥት ስር እስካለን ድረስ ለዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት በሚደረገው ሰላማዊና ሕጋዊ ተጋድሎ የምርጫ ሂደት ሊያደርግ ስለሚችለው እገዛ በሰፊው የኔንም ሆነ የድርጅቴን የመኢሶንን ሃሳብ ለማቅረብ ሞክሬያለሁ:: አመጽ ሳይሆን ሰላማዊ ሕዝባዊ ትግል፣ ለትርምስና ለወያኔ አንጃ ፕሮቮካትሮች ክፍተት እንዳይሰጥ የተደራጀና የተቀናጀ ትግል፣ በውስጥም በውጭም ተአማኒነት እንዲኖረው ግልጽ በሆኑ አማራጮች ዙሪያ የሚካሄድ ትግል... ባጭሩ በሂደቱ መልክ ያለው በውጤቱ ደግሞ ለመላ ኢትዮጵያውያን - ለኢሕአዴግ አባላትና ደጋፊዎች ጭምር ቦታ የሚሠጥ በዴሞክራሲና በብሔራዊ እርቅ ላይ የተገነባ ሥርዓት ለመገንባት ስለሚቻልበት ሁኔታ ያለኝን የኔንም የመኢሶን ታጋዮችንም ሃሳብ ሰንዝሬያለሁ:: በዚህ ከሁለት መቶ ገጽ በላይ በያዘ መጽሐፍ አንድም ቦታ ለትጥቅ ትግል ጥሪ የማደረግበት ቦታ የለም::

... በአመጽ የመጠቀም ሴራ ካለ የወያኔ ሴራ እንጂ የተቃዋሚዎች አይደለም:: እኛ ሕዝባችንን ይዘንና በሕዝባችን ፊት ተከራክረን አሳምነን ይህንን ሕገ መንግሥት እንጠብቃለን አይሉም:: በአመጽ እንሰማራለን ባዮች ናቸው:: ግን ይኼም የማያዋጣ እንደሆነ ያውቃሉ:: ብርክ የያዛቸው የሚመስለው ለዚህ ነው:: ለምን? እነሱም ሆኑ ፈረንጆቹ ይህ ሕገ መንግሥት ካልተስማማችሁ ትጥቅ ትግል አትበሉ እንጂ በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ዘዴ ማሻሻል መቀየር ይቻላል ባዮች ናቸው:: በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሕገ መንግሥት መቃወምና እንዲሻሻል ወይም ጨርሶ እንዲቀየር በሰላማዊ ዘዴ መታገል ያለ ነገር ነው:: አሜሪካ ባለፉት ሁለት መቶ ዓመታት ከሃያ ጊዜ በላይ ሕገ መንግሥቷን አሻሽላለች:: ፈረንሳይ የሄድን እንደሆነ «ማሻሻል» ብቻ ሳይሆን በሪፑብሊክ ደረጃ እንኳን አንደኛው ሪፑብሊክ፣ ሁለተኛው ሪፑብሊክ እያለች ጠቅላላውን ሕገ መንግሥቱን እየቀየረች አሁን አምስተኛው ሬፑብሊክ ስር ነች:: ዛሬ ደግሞ ይህንን ተቃውመው ለስድስተኛው ሪፑብሊክ የሚታገሉ ኃይሎች አሉ:: ዋናው ነገር ይህ መሻሻልም ሆነ መቀየር በሰላማዊና በሕጋዊ ትግል መካሄዱ ነው:: መጽሐፉም ላይ ያልኩት ይህንኑ ነው::

ሰዎቹ ስለ አመጽ ሴራና ስለትጥቅ ትግል ሕብረተሰቡን ለማስፈራራት ቢሞክሩ የዚህ ምክንያቱ ግልጽ ነው:: ይህንን ሕገ መንግሥት እኛ አንድና አንድ ሁለት ነው እንደማለት ቀላል በሆነ ትንተና ለምን «የሌላ ዘመን» ሕገ መንግሥት እንደሆነ፣ ለምን ሀገሪቱን ለአምባገነናዊ አገዛዝ እንደሚዳርግ፣ ለምን ለሀገራችን አንድነትና ለሕዝባችን ሰላም አደገኛ ሰነድ እንደሆነ ማሳየት እንችላለን:: እነሱ ግን ይህ ሕገ መንግሥት ዴሞክራሲያዊ ነው ብለው ወንዝ የሚያሻግር መከራከሪያ ማምጣት ስለማይችሉ በጉዳዩ ክርክር እንዲደረግ ጨርሶ አይፈልጉም::

ጦቢያ:- እየተከራከሩ ናቸው እኮ:: በሀገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ገንብተናል:: ይህንን ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ለማፍረስ በዶክተር ነገደ የተጠነሰሰና ተቃዋሚዎች ያፀደቁት ሴራ አለ ብለው አያቆሙም:: እንዲያውም ይህንን ሴራ ለማክሸፍና ሕገ መንግሥታችንን ለመጠበቅ ማንኛውንም አስፈላጊ የሆነ እርምጃ ከመውሰድ አንመለስም እያሉ እኮ ነው?

ዶ/ር ነገደ:- እስካሁን በሕገ መንግሥቱ ይዘት ላይ አይደለም የሚከራከሩት:: ነገም ቢሆን አይችሉም:: በኔ እምነት እንዲያውም ሴራ ሴራ የሚባለው ከዚህ ክርክር ለመሸሽ ነው:: በዚህ በሕገ መንግሥት ጥያቄ በመጽሐፉ የተስተጋባው አቋም ባጭሩ ምንድን ነው? ዛሬ አገራችን የምትተዳደርበት የበላይ ሕግ እንደ ሰሜን ኮርያ ዓይነት እፍኝ የማይሞሉ አገሮች ብቻ በቀረ «ስታሊናዊ ሕገ መንግሥት በቴምሪና በተግባር» ለሚባል የሕገ መንግሥት ኮርስ ለናሙናነት ሊቀርብ የሚችል ሰነድ ነው:: እንደማንኛውም ስታሊናዊ ሕገ መንግሥት ገና ከጥንስሱ የአንድን ፓርቲ የፖለቲካና የርእዮተ አለም እይታ እንዲሁም የኢኮኖሚ ምርጫ የሀገሪቱ የበላይ ሕግ ለማድረግ ሆን ተብሎ የተበጀ ሰነድ ነው::

ሂደቱን እንመልከት:: በመጽሐፌ ላይ ሕገ መንግሥቱን ያጸደቀው ሸንጎ «የኢሕአዴግ ኮርጆ ታዊ ጉባኤ» መልክ ነበረው እላለሁ:: የተሰየመው የነፃ ምርጫ መሥፈርቶችን በምንም «መሥፈርት» በሚያሟላ ሂደት አልነበረም:: ይባስ ተብሎ ደግሞ በዚህ ምርጫ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን የዜግነት መብታቸውን ተነፍገው በሂደቱ እንዳይሳተፉ ተደርገዋል:: በነገራችን ላይ መጽሐፉ ላይ እንደሚታየው ይህ ዜጎችን ከምርጫ ሂደት የማግለል ሂደት የሦስቱም የተፈራረቁብን ሥርዓቶች ቋሚና የጋራ ገጽታ ነው:: በአፄ ኃይለ ሥላሴ የመጀመሪያው የምርጫ ሕግ በሂደቱ የሚሳተፉት ፊውዳሎች ብቻ ነበሩ:: የምርጫው ሕግ አንቀጽ 30 የመምረጥና የመመረጥን መብት ለየአካባቢው መኳንንት፣ ቀሳውስትና የጦር አበጋዞች ብቻ ሰጥቶ እንዲያውም ከዚህ አልፎ ድሃው ገበሬ ቀርቶ «ብገን

⇨

ዘብ ብቻ የከበሩ ተርታ ሰዎች እንዳይወዳደሩ ክልክል ነው» ይል ነበር። ማለትም በመደብና በኢኮኖሚ መሥፈርት ተነስቶ ባለ ሁለት ማዕረግ ዜግነት ይደነግግ ነበር ማለት ነው። በደርግ ደግሞ ከኢሠፓ አባላት ውጭ ሌሎች ዜጎች ሊወዳደሩ የሚችሉበት ሁኔታ ስላልነበረ እሱም በፖለቲካ መሥፈርት ዜጐችን በሁለት ማዕረግ የሸነሸነ ሥርዓት ነበር። ወያኔ ይባስ ብሎ ሦስተኛ ማዕረግ ጨምሮልናል። ማለትም የመምረጥም የመመረጥም መብት ያላቸው አንደኛ ማዕረግ ዜጐች፣ በብሔርና ቋንቋ መሥፈርት የመምረጥ እንጂ የመመረጥ መብታቸውን የተነፈጉ ሁለተኛ ማዕረግ ዜጎችና በፖለቲካ መሥፈርት የመምረጥም የመመረጥም መብት ያልነበራቸው የቀድሞ የኢትዮጵያ ሠራዊትና የኢሠፓ አባላት እንዲሁም በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሦስተኛ ማዕረግ ዜጎች። በዚህ ሁኔታ ይህ ምርጫ የተካሄደው ቢያንስ ቢያንስ አምስት ሚሊዮን ዜጎች ሙሉ የዜግነት መብታቸውን በተነፈጉበት ሁኔታ ነበር ማለት ነው። በመሆኑም ከ547 አባላቱ በሦስት ተቃዋሚና 7 ድምፅ ያልሰጡ ፀደቀ የተባለው ሰነድ በሃቀኛና ሕብረተሰቡን በሙሉ በሚወክል ሸንጎ ሳይሆን የኢሕአዴግ ጠቅላላ ጉባዔ መልክ ባለው አካል ነበር ማለት ነው።

ይዘቱን በተመለከተ ይህ ሕገ መንግሥት እንደ ቀደመው የደርግ ሰነድ «በመደብና ወገናዊ ራዕይ» ላይ የተገነባ ነው። የዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት የማዕዘን ድንጋይ የሥልጣን ክፍፍል መርህ የሆነውን ያህል ትላንት የመንግሥቱ፣ የሶቭየትና የሕዝባዊ ዴሞክራሲዎች ዛሬ ደግሞ የቻይና፣ የኩባ፣ የቪየትናም፣ የሰሜን ኮርያና... የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት የማዕዘን ድንጋይ የሥልጣን አንድ ወጥነት ቴዎሪ ነው።

በዚህ ቴዎሪ መሠረት ሥልጣን ተከፋፍሎ ሳይሆን ተጠቅልሎ ለአንድ «ከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣን አካል» ይሰጣል። ትላንት የሶቭየት ሕብረት ሕገ መንግሥት አንቀጽ 108 «በሶቭየት ሕብረት የመንግሥት ሥልጣን ከፍተኛ አካል ሶቭየት ሱፕሪም ነው» ይል ነበር። ደርግ ደግሞ አንቀጽ 62 «በኢሕድሪ የመንግሥት ሥልጣን ከፍተኛ አካል ብሔራዊ ሸንጎ ነው» ይል ነበር። ዛሬ የሰሜን ኮርያ አንቀጽ 87 «በኮርያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲዊ ሪፐብሊክ የመንግሥት ሥልጣን ከፍተኛ አካል ከፍተኛው የሕዝብ ምክር ቤት» ነው ይላል። የኢሕአዴግ አንቀጽ 50/3 ደግሞ «በኢፌዴሪ የመንግሥት ሥልጣን ከፍተኛ አካል የተወካዮች ምክር ቤት ነወ» ይላል።

ዛሬ በሀገራችን ማ ይሙት እስቲ ማነው ይህ የነ አቶ መለስ አሻንጉሊት የሆነው ፓርላሜንት ከነ አቶ መለስ በላይ ነው ብሎ የሚያስብ ዜጋ? ማንም ያለ አይመስለኝም። እኔ በመጽሐፌ «ያጋለጥኩት» ምንም ሕዝባችን የማያውቀው ነገር የለም። ፓርላሜንቱ አሻንጉሊት ነው፣ የዳኝነት ነፃነትም ሆነ የሕግ የበላይነት የለም፣ እነ አቶ መለስ ከሕግ በላይ ናቸው ስል ያደረግሁት አንድ ነገር ቢኖር በሕግ ምሁርነቴ ከዚህ ሁሉም ከሚያውቀው ሃቅ በስተጀርባ ያለውን ስታሊናዊ ቴኦሪ ነው።

ሕገ መንግሥታቸው የተገነባበት የመንግሥት ሥልጣን አንድ ወጥነት ቴኦሪ እንዴት በቀጥታ ወደ አንድ ክሊክ ወይም ግለሰብ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ያመራል? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ሞክሬያለሁ። እዚህ ላይ ባጭሩ ልመለስበት። የመንግሥት ሥልጣን ክፍፍል መርህ የሚሠራበት ሜካኒዝም የአግድሞሽ የሥልጣን ድልድል (ሆሪዞንታል ዲስትሪቡሽን ኦፍ ፖዎር) አሠራር ይከተላል። ከፍተኛ የመንግሥት አካል የተባለው ፓርላሜንት ሥልጣንን ለገኘው ፓርቲ፣ ገኘው ፓርቲ ደግሞ «በዴሞክራቲክ ማዕከላዊነት» መርህ ሥልጣኑን ለማዕከላዊ ኮሚቴው፣ ይህ ደግሞ ለፖሊት ቢሮው፣ ይህ ደግሞ መልሶ ለጥቂት ሰዎች ወይም እስከናካቴው ለአንድ ግለሰብ «ውክልና» በመስጠት በቀጥታ ወደ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ያመራል። ለዚህ ነው ትላንት መንግሥቱ/ኢሠፓ ዛሬ ደግሞ መለስ/ኢሕአዴግ የሀገሪቱን የዳኝነት፣ የሕግ አውጪነት፣ የሥራ አስፈጻሚነትና የሕገ መንግሥት ቁጥጥር ተግባራት በሙሉ ለመቆጣጠርና ከሕግ በላይ ሆነው ለመግዛት የቻሉት። ሁሉም ይህ ሕገ መንግሥት የደደቢቱ የወያኔ ፕሮግራም ነው ይላል። እኔ በዚህ ላይ «ያጋለጥኩት» ይህንን ሃቅ መናገር ሳይሆን ከዚህ ክስተት ጀርባ ያለውን «ፖዚቲቪዝም ፕሮግራማቲክ» የተባለውን የሶቭየት ሕገ መንግሥት ቴዎሪ  ሌላ የማዕዘን ድንጋይ ነው። ሌላ ነገር የለውም። በመጽሐፉ ይህንን ሁሉ በዝርዝር ለማሳየት ሞክሬያለሁ። ይህ ሕገ መንግሥት እዝችም እዛችም  ይህንን ወይም ያንን አንቀጽ «በማሻሻል» ሳይሆን በሰላማዊ፣ ሕዝባዊና ሕጋዊ ትግል ከነፍልስፍናው ከአንቀጽ 50 ጋር መቀየር አለበት የምለው።

በወያኔ/ኢሕአዴግ በኩል በዚህ ጥያቄ ላይ ምንም ዓይነት ክርክር መግባት እንደማያዋጣቸው ስለሚያውቁ ደፍረው አይገቡበትም። ዳር ዳሩን በሌሎች ባልተባሉ ጉዳዮች ላይ ውይይቱ አቅጣጫ እንዲስት ይፈልጋሉ። ይህ ሕገ መንግሥት በሥልጣን አንድ ወጥነት ሳይሆን በሥልጣን ክፍፍል መርህ ላይ የተመሠረተ ነው ብለው ሊከራከሩ አይችሉም። የነሱ አንቀጽ 50 የትላንቱ የደርግ አንቀጽ 62 የዛሬው የሰሜን ኮርያ አንቀጽ 87 ፎቶ ኮፒ ቢሆን «አጋጣሚ» ነው ሊሉ አይችሉም። ባጭሩ ይህ ሕገ መንግሥት ስታሊናዊ አይደለም ዴሞክራሲያዊ ነው ብለው ሽንጣቸውን ገትረው ሊከራከሩለት አይችሉም።

ጦቢያ:- ኢሕአዴግ በይፋ በዶክተር ነገደ መመሪያ መሠረት ሕብረቱና ተቃዋሚዎች «ሕገ መንግሥታዊውን ሥርዓት ለማፍረስ» እየተንቀሳቀሱ ነው እያለ «ማፍረስ» የሚለውን ቃል ይደጋግማል። ውስጥ ውስጡን ግን በተለይ ለአባላቱ፣ ለሠራዊቱ፣ ለካድሬዎቹ የሚነዛው ሌላ አስፈሪ ፕሮፓጋንዳ ነው። ደርግ ንጉሡን ሲጥል እንዳደረገው፣ እኛም ደርግን ጥለን መንግሥት ስንቆጣጠር እንዳደረግነው አሁን ተቃዋሚዎች እኛን አሸንፈው ሥልጣን ቢይዙና «ሕገ መንግሥታችን ቢፈርስ» ድርጅታችንም ይታገዳል፣ ሠራዊታችንም ይበተናል፣ ስለዚህ ለሳው ቢቀር ለሕልውናችሁ ታገሉ በሚል ቅስቀሳ ተሰማርቷል። እርስዎ ሕገ መንግሥቱን «ለማስወገድ» ሲያወሩ ይህንን የኢሕአዴግ ፕሮፓጋንዳ አያግዙ አይደለም ወይ?

ዶ/ር ነገደ:- በፍጹም አይደለም። እንዲያውም ከዚህ ድርጅት መሪዎች ጋር ያለንን የራዕይ ልዩነት ሰፋት ከሚያሳዩት ጉዳዮች አንዱ ይህ ነጥብ ይመስለኛል። የእነሱ ዶሮ ብታልም ያን ጥሬዋን ነው። የመጣ ቢመጣ ጭንቀታቸው ይቺ በሆነ የታሪክ አጋጣሚ የተቆጣጠሯት ሥልጣን ከእጃቸው እንዳታፈተልክ ብቻ ነው። እኛ የምናወራው ለነሱም ለኛም ስለምትሆን ኢትዮጵያ፣ ለነሱም ለኛም ስለሚሆን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ ለመላው ሕብረተሰባችን በዚህ ዴሞክራሲ ብቻ ሳይሆን በብሔራዊ እርቅ ፖለቲካ የተረጋጋ ኑሮ ስለምናረጋግጥበት ሁኔታ ነው። በቅርቡ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት (ኢዴኃህ) ይፋ ባደረገው አማራጭ ሰነዳችን ለዚህ ለብሔራዊ እርቅ ጉዳይ ሰፊ ቦታ ሰጥተነዋል። በቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ዙሪያ የተሰማሩት ወገኖቻችንም እንደኛው ሰፊ፣ እርቆ አስተዋይና አገራዊ ራዕይ ስላላቸው ለዚህ ጉዳይ በማኒፌስቷቸው ሰፊ ቦታ ሰጥተውታል። በኔ ግምት በተደራጁ ተቃዋሚ ኃይሎችም ሆነ ከድርጅት ውጭ ባሉ ዴሞክራቶችና በአገር ወዳድ ኃይሎች መካከል እንደዚህ ጥያቄ ሰፊ ድጋፍ ያለው አጀንዳ ያለ አይመስለኝም። ይህ ደግሞ ከሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች የመጣ ይመስለኛል። አንደኛው ምክንያት ካስከፊው የአመጽ፣ የትርምስና የቂም በቀል ታሪካችን የቀሰምነው ትምህርት ይመስለኛል። ሁለተኛው ደግሞ ለዚህ አገርና ለዚህ ሕዝብ ዕጣ ፈንታ ያለን ብሩህ ህልም ነው። የኔ ጭንቀት እስከዚህም ቀጣዩ ምርጫ ሳይሆን ለሀገራችን ለቀጣዩ ክፍለ ዘመን አንድ ፕሮጄ ወይም ርዕይ ይኑረን የሚል ስለሆነ በሰጣችሁኝ አጋጣሚ ትንሽ ሰፋ አድርጌ ሃሳቤን ልግለጽ።

ስላለፈው በአመጽ የተበከለ የታሪክ ሂደት በመጽሐፌ በሰፊው አትቻለሁ። በቅርቡ ጊዜ ታሪክ ተወስነን ከዘመነ መሳፍንት ወዲህ እንኳን ያለውን ሁኔታ ስንመለከት በነዚህ ሁለት መቶ ሃምሳ ዓመታት አገራችን በተከታታይ የአስር ዓመት ሠላም አግኝታ አታውቅም። በነዚህ ዓመታት ሕዝባችን አገኘ የሚባለው ሠላም ሁልጊዜም አሸናፊዎች በሥልጣን ተቀናቃኞቻቸው ላይ ብቻ ሳይሆን ሕብረተሰቡን በሙሉ ያሸነፉ ይመስል በሕዝባችን ላይ የጫኑት የአሸናፊዎች ሠላም ነበር። አሁንም ነው። ከነዚህ ከማያባሩ ግጭቶች ሕብረተሰባችን በሙሉ እንዳለ በድል አድራጊነት የወጣበት አንድም ወቅት የለም። «ሠላም በድል» እንጂ «ሠላም በእርቅ» የሚባለው ፅንሰ ሃሳብ በዚህ በዘመናት ትርምስ የአመጽ ባህል ባካበተ ሕብረተሰብ ውስጥ ጨርሶ የሰረፀ አልነበረም። ላለፉት አስር ዓመታት በመኢሶን በኩል በተለይ ፓሪስ አንድ፣ ፓሪስ ሁለት፣ አማራጭ ኃይሎች፣ ኢተፖድን እያልን፣ የተለያዩ ሰነዶችን እያቀረብንና እያስፀደቅን ሳናሰልስ ስንታገል የቆየነው ይህ የእርቀ ሠላም አዲስ መንፈስ በሕብረተሰባችን ውስጥ እንዲሠርጽ ነበር። ዛሬ ከኋላ ቀሮቹ ከወያኔ/ኢሕአዴግ መሪዎች በስተቀር ይህ አሸናፊን ወደ ቤተ መንግሥት፣ ተሸናፊን ደግሞ ወደ ወህኒ ቤት ወይም ወደ ጫካ እየላከ ሕብረተሰቡን በሙሉ የድል አድራጊዎች እስረኛ አርጎ የሚይዘው አጥፊ አዙሪት በመላው በሕብረተሰባችን የተተፋ ባህል ነው። ይህ አዙሪት ለአንዴም ለዘላለሙም ተሰብሮ በዚህ ባልተቋረጠ ትርምስ ፋታ ተነስቶ የደም እንባ ያነባውና ጀርባው የተላጠው ሕዝባችን እፎይ እንዲልና ይችን ገኘዎች ያንክራከሷትን ታላቅና ሀብታም አገሩን መልሶ ወደ መገንባቱ እንዲያተኩር እንፈልጋለን። ይህንን በኢዴኃህ ፕሮግራማችን በግልጽ አስቀምጠነዋል። ማንም ዜጋ የኢሕአዴግ አባል፣ መሪ፣ ደጋፊ ነህ ወይም ነበርክ ተብሎ እንኳን ሊታሰር፣ ሊንገላታና ከሥራ ሊባረር ቀርቶ ዝንቡንም እሽ የሚል ማንም አይኖርም።

ሁላችንም ማለትም የኢሕአዴግ መሪዎች ጭምር ቆም ብለን እናስብ። ስለ ቀጣዩ ክፍለ ዘመን እናውራ ስል ያለፈውን ወይም በማለፍ ያለ ያለውን ክፍለ ዘመንም ሂደታችንን እንንቃኝ ማለቴ ነው። ፓሪስ በአንድ ስብሰባ ላይ ኢትዮጵያን በተመለከተ ይህንን ክፍለ ዘመን «የኪሳራ ክፍለ ዘመን» (ሲየክል ኢንዩቲል) ብዬ ጠርቸዋለሁ። ሰሞኑን በዚህ ጉዳይ እነ ዶክተር መሳይ ከበደ ያነሳሱት አንድ ቁም ነገር ያዘለ ውይይት በኢንተርኔት እየተካሄደ ነው። ክፍለ ዘመኑን ስንጀምር የውቅቱ ምሁራን እነ ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝና ሌሎችም ለሀገራችን ለውጥ፣ ሠላም፣ ሥልጣኔና ዴሞክራሲ ብለው ጀምረዋል። ዛሬ ከመቶ ዓመት በኋላ  በሠላምም፣ በበጎ ለውጥም፣ በዴሞክራሲም ገና ነን። ይህ ለምን ሆነ? ለሚለው ጥያቄ አንዳንዶቹ የሚሰጡት መልስ የተፈለገው «ሥልጣኔ» የአውሮፓን ሥልጣኔ እንዲያማክል (ዩሮ ሴንተርድ) ሆኖ ስለታለመ ነውና ከዚህ ይልቅ ተመልሶ በኢትዮጵያ እሴቶች ላይ የተማከለ የለውጥ ወይም የሥልጣኔ አቅጣጫ መያዝ አለበት የሚል ሃሳብ ነው።

⇨

እርግጥ መጭው ሥልጣኔያችን በኛው እሴቶች ላይ የተገነባ መሆን እንዳለበት ምንም ክርክር ሊኖር አይችልም:: ለእኔ ዋናው ችግር «የአውሮፓን ሥልጣኔ» የመቅዳት ያለመቅዳት ችግር አይደለም:: እነ ጃፓን እነ ቻይናና ሌሎችም አገሮች ከአውሮፓ ወይም ከዘመኑ ሥልጣኔ የሚሆን የሚሆነውን የወሰዱ በእሴቶቻቸው ላይ እየገነቡ ሲራመዱ አይተናል:: የኛ ችግር እንደሚመስለኝ የምንወስደው ሁሉ «የማይሆን የማይሆነውን» መሆኑ ነው:: አፄ ቴዎድሮስ የሀገሪቱን «የኢንዱስትሪያላይዜሽን» ጥረት ለምን በነገሱበት ዓመት በአውሮፓ ተካሂዶ እንግሊዞችና ፈረንሳዮች ድል ባደረጉበት ከተማ ስም «ሴባስቶፖል» ብለው የጠሩትን መድፍ በማሠራት ጀመሩ፣ በኋላስ በክፍለ ዘመኑ መጀመሪያ ላይ ለምን የጨርቃ ጨርቅ፣ የሳሙና፣ የጫማ ፋብሪካ ሳይሆን ተሸቀዳድመን ጥይት ፋብሪካ ማቋቋም ላይ ተሰማራን? በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን የተደረገው ሀገሪቱን «ዘመናዊ የማድረግ»» ጥረት እንዳለ ሕብረተሰቡን «ዘመናዊ» ከማድረግ ይልቅ ከአውሮፓ ሥልጣኔ ዘመናዊ ሠራዊት፣ ዘመናዊ የአየር ኃይል፣ ዘመናዊና በዘመናዊ መሣሪያዎች የሚገለገል ፖሊስና ደህንነት፣ «ዘመናዊ የፕሮፓጋንዳ ተቋም መርጦ ለምን ዘመናዊና ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት» በማቋቋም ላይ አተኮረ? ይህንን ሕብረተሰቡን ሳያስከትል የሚደረግ «የዘመናዊነት» ሂደት እጅግ ኋላ ቀር በሆነ ፊውዳል ሕብረተሰብ እንዴትና ለምን ዘመናዊ የሆነ መንግሥትና ቢሮክራሲ ሆነ በሚል የዛሬ ሰላሳ ዓመት የዶክቶራል ቴዚን (ለዶክትሬቴ) ስሠራ አንስቼው ነበር:: ያኔ ርዕዮተ ዓለሙም፣ የወጣትነት ርግጠኛነቱና ድንፋታውም ተደማምረው «ሲምፕሊስቲክ» መልስ ነበረኝ:: ይህ ሁሉ የፊውዳሉ ሥርዓት ጥፋት ነው!! ከዚያ የሽግግር ዘመናት እየተባሉ የተፈራረቁብን ጊዜያዊ መንግሥታት «ሽግግር» እያሉ ሕብረተሰቡን እየተው እነሱው ወደ ቋሚነት ሲሸጋገሩ ታዘብኩ:: ሌሎችም ጥያቄዎች መጡብኝ:: የደርግ መንግሥት ሶሻሊዝምን «ከአውሮፓ ሲቀበልና» የወዝአደሩ የበላይነት ብሎ የፖለቲካ ነፃነትን ሲያፍን ይህንን አፈና እንደተቀሩት ሶሻሊስት አገሮች ጤና ለሁሉ፣ ሥራ ለሁሉ፣ ትምህርት ለሁሉ በሚሉ ማህበራዊ መብቶች ማካካስ አቅቶት ለምን አገራችንን ከሁለት ያጣች ጎመን አደረጋት? ዛሬስ ቢሆን የወያኔ ኢሕአዴግ አገዛዝ «ከዘመኑ ሥልጣኔ» ነፃ ገበያ ብሎ ሊቤራሊዝምን ሲቀበል በፖለቲካው መስክ ግን ለምን በሊቤራሊዝም ሳይሆን በአፋኙ «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» ፍልስፍናና በስታሊናዊ ሕገ መንግሥት ጎዳና ተሰማራ?

እነዚህን በርካታ ጥያቄዎች እያነሱ መወያየት ያስፈልጋል:: እኔም ወደፊት በሰፊው እመለስበታለሁ ብዬ ተስፋ አለኝ:: እዚህ ላይ ግን ከፍ ተብሎ ወደተነሳው ጥያቄ ልመለስና ከዚህ «ለውጥ፣ ሠላም፣ ዴሞክራሲ» እያልን ከኩዋተንዝብት ከአንድ ክፍለ ዘመን በበኩሌ የቀሰምኩት ትምህርት የክፍለ ዘመኑ አካሄዳችን ሶስቱን እሴቶች እያስተጋገዘን ሳይሆን እርስ በርስ እያጠፋፋን መጓዛችን ነው የሚለው ትምህርት ነው:: ለቀጣዩ ክፍለ ዘመን ፕሮግራሙ ወይም ራእይ ስል ያለንበትን የሶስቱን የእርስ በእርስ መጠፋፋት አዙሪት ሰብረንና የሚተጋገዙበትን በጎ አዙሪት ቀስቅሰን እንዴት አገራችንን የእድገት፣ የፍትህ፣ የሠላም ጎዳና እናስይዛት የሚለውን ጥያቄ ተወያይተን እንመልስ ማለቱ ነው:: ይህንን አዙሪት ለመስበር የመጀመሪያ መጀመሪያው ተግባርና ኃላፊነት በብ ሐራዊ እርቅ ፖሊሲ የተረጋጋ ሕብረተሰብ መሠረት መጣል ነው:: ይህ ደግሞ የኢ.ሕአዴግንም አባላት የሚጨምር ሂደት ነው::

የኢ.ሕአዴግ መሪዎች የተለከፉበት «ተቃዋሚዎች ስልጣን ከያዙ ያልቅላችኋል» የሚለው የሽብር ፈጠራ ዘመቻ በኛ በኩል ምንም ተቀባይነትም የማይኖረው ለዚህ ነው:: ለዚች አገርና ለዚህ ሕዝብ ዕጣ ፈንታ ብሩህ የሆነ ህልም ያለን ታጋዮች ነን:: ትግላችን መሥዋእትነታችን በዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥታዊ ስርዓት ማንም ከህግ በላይ ሆኖ የማይከበርበት፣ ማንም መብት አልባ ሆኖ የማይናቅበት፣ ማንም ግለሰብ ሰው ሆኖ በመፈጠሩ ብቻ የሚላበሳቸውን መብቶች በሙሉ የሚረጋገጥበት፣ ማንም ኢትዮጵያዊ የዚች አንድ እናት አገራችን ዜጋ ሆኖ በመፈጠሩ ብቻ የሚጠብቀውን የዜግነት መብት ተጎናፅፎና የሚጠበቅበትን የዜግነት ግዴታ እየተወጣ በሠላም ኮርቶ የሚኖርባት አገር ለመገንባት ነው:: በዚህ ሥርዓት ውስጥ ኢሕአዴግ ቦታ ይኖረዋል:: ሕዝብ በፓርላማ አብላጫ ድምጽ ከሰጠው ወይም ከሌላ ድርጅት ተጣምሮ ከቻለ በመንግሥትነት ይቀጥላል:: ይህንን ካልቻለ ደግሞ እስከ ቀጣዩ ምርጫ በተቃዋሚነት ተከብሮ የሚኖርበት ሥርዓት ነው የምንፈልገው::

ጦቢያ:- ወደ ሕገ መንግሥቱ ውይይት እንመለስ:: እነሱ በተደጋጋሚ ምንም የማይወጣለት ዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግስት ነው ሲሉ እርስዎ ደግሞ በመፅሃፉ ላይ በተደጋጋሚ ይህንን ሕገ መንግሥት ከደርግ ዘመን ሕገ መንግሥት ከዚያም አልፈው ከሰማን ኮርያ ሕገ መንግስት ጋር ያመሳስሉታል:: ትላንት ከደርጉና ከንጉሡ ዘመን፣ ዛሬም ከሰማን ኮርያ የላቀ ነፃነት በሃገራችን እንዳለ መካድ ይቻላል ወይ?

ዶ/ር ነገደ:- እርግጥ ነው ዛሬ በአገራችን ካለፈው ከደርግ ዘመን ከነበረውና ዛሬ ከሰሜን ኮርያ ካለው የተሻለ ነፃነት አለ:: ግን ዞሮ ዞሮ የተጫነብን ሕገ መንግሥት ፍልስፍናው፣ የማእዘን ዲንጋዩና አሠራሩ ከነዚህ ከሁለቱ ጋር አንድ ስለሆነ ከዴሞክራሲ ገና የትየለሌ ነን:: ነፃነት መናገር ስትችል ነው:: ዴሞክራሲ ተናግረህ የሚያዳምጥ ስታገኝ ነው:: ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ላንቃው እስኪሰነጠቅ ይጮሃል:: ወያኔ ቀርቶ «የልብ ትርታውን እንከተላለን» የሚሉት ተቃዋሚዎችም እንኳን በቅጡ የሚያዳምጡት አይመስለኝም:: ሕዝብን ማዳመጥ በሌለበት ሁኔታ ደግሞ ዴሞክራሲ ማለትም የሕዝብ ፈቃድና ፍላጐት የበላይነት የሚጎናፀፉበትና በተግባር የሚተረጎምበት ስርዓት በምንም ተአምር አይኖርም:: በተሻለ መናገር ይቻላል ብሎ ስለተናገረ፣ ሰላማዊ ሰልፍ ይቻላል ተብሎ ሰልፍ ስለወጣ ቀርቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ በምርጫ 51% አምጥቶ ስልጣን ቢይዝ እንኳን ፈቃዱ የሚደመጠበት ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ውስጥ አይደለንም:: ላብራራ::

በደርግ ዘመን የማይችለውን ዛሬ ሕዝቡ የመንግስትን ፖሊሲ ተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ ሊወጣ ይችላል:: ተቃዋሚዎች በተደጋጋሚ ሕዝቡን ያሰልፉታል:: ሕዝቡም ተሰልፎ፣ ብሶቱን አሰምቶ ቤቱ ይገባል:: የሕዝብ ተደማጭነት (ማለትም በሌላ አነጋገር የመንግሥት ተጠያቂነት) ያለበት ሥርአት ቢኖር ኖሮ የኢ.ሕአዴግ መንግስት ዛሬ ሕዝብ በ100ሽ እየተቆጠረ የወጣው ምን ጠይቆ ነው? ብሎ ይህንን ጥያቄ ለማስተናገድ ይሞክር ነበር:: ይህንን ከማድረግ ይልቅ የሚቀናው «ይኸው በአዲሱ ዴሞክራሲያዊ ስርዓቴ ሕዝቡ በመቶ ሺህ እየተቆጠረ ለተቃውሞ ሰልፍ መውጣት ይችላል» በሚል ፕሮፓጋንዳ መመፃደቅ ነው:: ታዲያ ማንም «ይህንን የሕዝብ ጥያቄ ለማስተናገድ ምን አደረግህ» ብሎ የሚጠይቀው የለም::

በደርግ ዘመን በሌለ ሁኔታ ዛሬ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በይፋ ተመዝግበው መንቀሳቀስ ይችላሉ:: ማለትም ነፃነት አለ:: በነገራችን ላይ እስካሁን ደፍሮ የተደራጀ የለም እንጂ የሰሜን ኮርያም ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 67 ላይ የፖለቲካ ድርጅቶች ይፈቅዳል:: እኛ አገር ተቃዋሚዎች ከመመዝገብም አልፈው ስልጣን ለመያዝ በምርጫ መሳተፍ ይችላሉ:: ይህንን ከፊት ያለ ሁኔታ ኢ.ሕአዴግ በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ መድበለ ፓርቲ ሥርአት መሠረትሁ በማለት ይመፃደቅበታል:: ነገር ግን ያለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ምንድነው? እዚህም ላይ እንደ ሰላማዊ ሰልፉ ነው:: ከፍ ብየ እንዳልኩት ሕዝባችን በምርጫ ተሳትፎ በፓርላማው ውስጥ አብላጫ ድምጽ አግኝቶ የመንግስት ስልጣን ቢይዝ እንኳን ይህንን ነፃነት ወደ ተደማጭነት መቀየር አይችልም:: መሬት መሸጥ መለወጥ መቻል አለበት በሚል ፕሮግራም የሕዝብ ድጋፍ አግኝተው የመንግስት ሥልጣን የሚይዙ ኃይሎች በፓርላማ ካለው መቀመጫ 51% ስላመጡ ብቻ ይህንን ፕሮግራማቸውን ማለትም ይህንን የብዙኃኑን ፈቃድ በተግባር ሊያውሉ አይችሉም:: ከፍ ብዬ ያልኩትን ልድገመውና ሕዝባችን እንኳን ተናግሮና ተሰልፎ ቀርቶ በዴሞክራሲያዊ ሂደት ምርጫ አሸንፎ መንግሥት ቢይዝ እንኳን ፈቃዱ የሚደመጥበት ሕገ መንግስታዊ ሥርዓት ውስጥ እንዳይደለን ግልጽ ነው::

ይህ ስለተባለ ባለው የመናገር ነፃነት ተጠቅመን አንናገር፣ ባለው የመፃፍ ነፃነት ተጠቅመን አንፃፍ፣ ባለው ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነት ተጠቅመን ሰልፍ አንውጣ፣ ባለው የምርጫ ሂደት ተጠቅመን ምርጫ ውስጥ አንሳተፍ ማለት አይደለም:: ባለው ፍንጭ ሁሉ መጠቀም ያስፈልጋል:: ዋናው ቁም ነገር ሕዝባችን ተናግሮና ተሰልፎ፣ ድምጽ ሰጥቶና የሚደግፋቸውን ኃይሎች ለሥልጣን አብቅቶ ፈቃዱ የሚፈፀምበት፣ ተደማጭነቱን የሚያረጋግጥበት ዴሞክራሲያዊ ሥርአት መሰረት ለመጣል መታገል አለበት:: ይህንን ለሕዝባችን አፍረጥርጠው ሳይናገሩ፣ ይህንን የጋራ ዴሞክራሲያዊ ሥርአት መሠረት ለመጣል በጋራ ተንቀሳቅሰው ሕዝባችንን በጋራ ከዳር እስከዳር ለማንቀሳቀስ ሳይንቀሳቀሱ «ግድ የለም እኛን ምረጥና ይቺን አገር የምድር ገነት እናደርጋለታለን» የሚሉ ኃይሎች እኔ በጣም ነው የሚቀፉኝ:: እነዚህ ወገኖቻችን በሕዝቡ ብሶትና የለውጥ ጥማት ተጠቅመው የግል ወይም የድርጅት አጀንዳ እንጂ የአገርና የሕዝብ ራእይ እያራመዱ አይደሉም:: መናገር ለመናገር ከሆነ፣ ሰልፍ መውጣት ዝም ብሎ ሰልፍ ለመውጣት ከሆነ፣ ምርጫ ውስጥ ተሳትፎ ወዴት ለመሄድ? እንዴት ለመሄድ? የሚለውን ጥያቄ በቅጡ ሳይመልሱ ለድርጅት ወይም ለግል መቀመጫ ለማግኘት ከሆነ በዚህ ሁሉ ከኛና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ይልቅ ይበልጥ ለፕሮፓጋንዳው የሚጠቀምበት ኢ.ሕአዴግ እንደሆነ በደንብ አርጎ መረዳት ያስፈልጋል:: ይህንን ካልተረዳን ትዟችን የእውር የድንበር ጉዞ ነው:: ይህንን ከተረዳን ደግሞ ዛሬ የትግላችን ዋና ዓላማ በመንግስት በኩል ተጠያቂነት በሕዝብ በኩል ደግሞ ተደማጭነትን የሚያረጋግጥ አዲስና ዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት እንዲሰፍን መጣር መሆን ይገባዋል:: ይህንን ጉዳይ በመጽሐፌ በሰፊው ስላብራራሁት ብዙም አልመለስበት::

ጦቢያ:- አዎን ግን እኮ ምናልባት ለኢሕአዴግ መንግሥት መከራከሪያ በር የከፈቱት ይህንን ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት በሰላማዊና ሕዝባዊ የትግል ማዕበል ማስወገድ ያስፈልጋል ብሉ «ማዕበል» የሚለውን ቃል ያነሱበት ክፍል ሲሆን አይችልም ወይ?

ዶ/ር ነገደ:- ይህንን ሕገ መንግሥት ለመቀየር የሚደረገው ትግል ሰላማዊ፣ ሕዝባዊና ሕጋዊ እንጂ በምንም ዓይነት በፀረ ሕገ መንግሥት ድርጊቶች የሚሰማራ እንደማይሆን በደንብ ሊሰመርበት ይገባል:: ከዚህ አልፎ ተርፎ ሕገ መንግሥቱ መቀየር አለበት ስላልን እነ አቶ በረከት እኔንም ሆነ መኢሶንን በአገር ማፍረስ ሴራ ሲወነጅሉ አንደኛ ነገር «አመድ በዱቄት እየሳቀ» እንደሆነ ግልጽ

ወደ ገጽ 13 ዞሯል